# የፓርላማ ተመራጭ የሆኑም ያልሆኑም የተቃዋሚ አባላት አዲስ ፓርቲ ሊያቋቁሙ ነው -(ኢፍቲን)

በ3ኛው አገር አቀፍ ምርጫ በቅንጅት ስም ተወዳድረው ለፓርላማና ለአዲስ አበባ ምክር ቤት የተመረጡ ቁጥራቸው 60 የሚደርሱ የመኢአድ፣ የኢዴሊ፣ የኢዴአፓ/መድህን እና የቀስተ ደመና አባላትና አመራሮች የሆኑት አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ እያቋቋሙ ነው (ኢፍቲን)።

አዲሱ ፓርቲ የማቋቋሙን ተግባር ለማከናወንም ካለፈው እሮብ ጀምሮ ምክክር ሲያደርጉ የቆየ ሲሆን፣ እነዚህ የአራቱ ፓርቲዎች አባላትና አመራሮች የነበሩ ሰዎች አዲስ ፓርቲ ወደማቋቋሙ ተግባር የገቡባቸው ዋነኛ ምክንያቶች፣ በፓርላማ ውስጥ ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተመራጮች እስከ አሁን ተወካይ የሌላቸው በመሆኑ ተመራጭ መምረጥ እንዲያስችላቸውና የአዲስ አበባ አስተዳደር ቻርተር «የከተማዋን ስልጣን አሸናፊው ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ይረከባሉ» የሚል በመሆኑ በዚህ መሠረት የአዲስ አበባ ተመራጮች የከተማዋን አስተዳደር ለመረከብ እንዲያመቻቸው እንደሆነም ተገልጿል።

የሚቋቋመው ፓርቲ አዲስ አላማና ኘሮግራም ይዞ የሚንቀሳቀስ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፣ በፓርቲው ስያሜና በፓርቲዎች ምዝገባ መመሪያና ደንብ መሠረት ከአምስት ክልሎች የ 1500 ሰዎች የድጋፍ ፊርማ የማሰባሰብ ተግባርን አስመልክቶ ውሳኔ ለማሳለፍ ዛሬ ውይይት እንደሚካሔድ ታውቋል።

አራቱ ፓርቲዎች ቀደም ሲል ለምርጫ ቦርድ ያቀረቡት የውህደት ጥያቄ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ይታወሳል።